Title: Nini Abino Interview

Creators: Abino, Nini; Bekele, Getnet

Date: August 15, 2010

City: Arsi Nagalle

Country: Ethiopia

African Oral Narratives: aodl.org/oralnarratives

ከጋሽ ኒኒ ጋር ተገናኝተን ስለ አርሲ ነገሌ እየተነጋገርን ነው ዛኔ ቀኑ ነሀሴ 7/2001 ዓ.ም. ነው፡፡

ይሄ የማሳይህ ወረቀት የግሚጅ እቴጌ ግዛት ወስጥ የወረዳ ግዛት ያለ የሜሬት ግዛትና ክፍፍል ሰንጠረዥ ነው፡፡

ጥ. እኚህ ሰው ብዙ እንደዚህዓይነት ወረቀት ይኖራቸው ይሆን እኔ ፎቶ ኮፒ አድርጌ ብወስድ

መ. እኔ ይሄ ስለሚያስፈልገኝ ነው የወሰድኩት ሊኖር ይችላል ሚጋገጥ እንችላለን፡፡

ጥ. አንዳንድ ሚጃዎች ያለታሰበ ቦታ ይገኛሉ ካለና የሚገኝ ከሆነ ይጠይቁልኛል

መ. እናጣራለን፡፡ በነገሌ ወረዳ 7 ባላባቶች ይገኛሉ እነርሱም እነሜራ፣ ኒኒ ፣ ማለዳ፣ዋጂ ዳዬ፣ እኛምሜ እሄቶታ ናቸው የሜሬት ክፍፍሉም -

- የግሚጅ እቴጌ ጋሻ 659 ተከል
- የገባር ባለርስት 479
- የሰሞን 67ጋሻ
- የባላባት ማጡሪያ 73 ጋሻ
- ስመጥሩ የኤርትራ ወያን 191.25 በድምሩ በወረዳው 1469.75 ጋሻ ሜሬት ነበር

ጥ. በጠቅላላው የነገሌ ጋሻ ርስት ስንት ይሆናል?

መ. 1469.75 ነው ከላይ የዘረዘርኩት በሙሉ እሱ ነው

ጥ. እነዚህ ባላባቶች በቱኬ ጊዜ የተሾሙናቸው?

መ. ቱኬ እኮ አገር ገዢ ነበሩ አርሲን ከብላቴ ወንዝ ጀምሮ እስከ ዋዜ ድንጋይ ይገዙ ነበር

ጥ. እነሾኒንም በእርሱ ስር ነው ያሉት?

መ. ሾኒ አይሻገርም ሾኒ የሚዛው ሀዲያ በጦሶ በላ ነው እርሱ ሀዲያና አላባን ይገዛል

ጥ. ሾኒ አሮሞ አይደለም እንዴ?

መ. ሾኒ ሀድያ ነው አፄ ምኒልክ በዘዴ ነው ያስቀማጡት ወላይታ በጦና ጋጋ ሀዲያ በገዲሳ በላ እነዚህ ባላባቶች ከ1923 ጀምሮ ነው የነበሩት

ጥ. ምን ያህለ ጋሻ ይገዛ ነበር ቱኬ ማማ ይህን ያከላል?

መ. ከዚህ ይበልጣል ከዋንዛበል እስከ ዋቤ በሰሜን እስከ አዋሽ ያለውን ነበር የሚዛው

ጥ. በሻሸሜኔ በኩል አድርገን አላባ ሄደን ከዛ የሻላን ሀይቅ አየነው እዛ ያሉት ሕዝቦች እነማናቸው?

መ. አላባዎችም አሮሞዎችም አሉ

ጥ. እነርሱ የምን አሮሞ ናቸው የአርሲ ወይስ የሊበን?

መ. የአርሲ አሮሞ ናቸው

ጥ. ቱኬ ማማ እነዚህ ሁሉ ያስተዳድር ነበር?

መ. አዎ ቱኬ መንግስትን እንዲጋራ ነበር በአርሲ አባ ገዳ የተሾመው

ጥ. ማን ነበር የአርሲ አባገዳ?

መ. ጂኖ ሮባ ይባላል ቱኬን የወከለው

ጥ. ቱኬ በዛን ወቅት ወጣት ነበር ማለት ነው?

መ. አዎ ወጣት ነው

ጥ. ጂኖ ሮባ ጎሳው ምን ነበር ከእነዚህ ወስጥ አንዱ ነው?

መ. ኢቤኖ ነው እነዚህን ሰዎች ለሹመት የሚያመጣው አባ ገዳ ነው ድሮ በምኒልክ ጊዜ በጎሳ እንዲስፋፉ የሚያደርገው አባ ገዳ ነው እንደመንግስት ድሮ አባ ገዳ እምነት ይጣልበታል

ጥ. በድሮ ጊዜ አባገዳ ከኤቢኖ ጎሳ ብቻ ነው የሚሾሚጠው?

መ. አባ ገዳ የሚሾሚጠው ከአንጋፋ ነው ሁሉም ጎሳ አባገዳ አለው ጠቅልሎ የሚይዘው ግን ኤቢኖ ነው የአርሲ ልጆች የመጀመሪያ ታላቅ እርሱ ነው፡፡

ጥ. በአርሲ ነገሌ ጎሳዎች መካከል አንዱ ኤቢኖ ነው ሌሎቹ እንማን ናቸው?

መ. ከስምንት በላይ ጎሳዎች አሉ ኤቢኖ ታላቅ ነው ኤቢኖ መሬትም የለወም ሀብትም የለወም እሱ መሬት እንዳያገኝ የሚያደርገው የአባ ገዳ ህግ ነው እርሱ ታላቅ ስለሆነ ሁሉም የእርሱ ነው፡፡

ጥ. ኤቢኖ ከግብር ነው ጥቅም የሚያገኝ ወይስ ከምን ነው?

መ. ምንም ግብር የለም በዓመት በዓል በሚከበርት ወቅት ሁሉም የሚያስፈልገው ያስገባሉ፡፡

ጥ. የያንዳንዱ ጎሳ አባ ገዳ ግን የጎሳው መሬት ባለቤት ነው ሀብቱ የእርሱ ነው?

መ. የመሬት ባለቤትነት አሁን በአፄ ሀ/ስላሴ ነው የመጣው ድሮ ይሄ ጋሻ የዚህ ነው የሚል የለም

በቱኬ ማማ ጊዜ ግብር የሚገበረው በመሬት ብዛት ነው አንድ መሬት ካለ አንድ ብር ነው ስፋት አይታይም

ጥ. ባላባቶቹ የመሬት ባለቤት የሆኑት በአፄ ሀ/ስላሴ ጊዜ ነው ማለት ነው?

መ. አዎ

ጥ. በድሮ ጊዜ ሰው የሚበላው ሚርና ገንፎ ነው ብላችኋል ገንፎው የምንድን ነው?

መ. የገብስ

ጥ. ገብሱ ከየት ይመጣል?

መ. ገብስ ድሮም አለ በኦሮሞ ወስጥ የሚዘራው ትልቁ እህል ገብስ ነው ገብስና ቡና ባያርሱም በልወጥ ያመጡሉ ለአምልኮ ሲሰበሰቡም ገብስና ቡና አይጠፉም

ጥ. ከአደዋ በፊት ነው ጎበና ይህንን አካባቢ ያስከበሩት ብለወኛል በግምት ከአደዋ 10 ዓመት በፊት ይሆናል?

መ. ይህን ያህል ለይቼ ባላወቅም በአደዋ ያልከብት በአደዋ ዘመቻ ከዚህ አካባቢ ሄደው የተዋጉ አሉ የኛ አባት ትልቅ ወንደምም ሄደው ተዋግተዋል ተርፈው መጥተው አዲስ አበባ ነበሩ

ጥ. ማን ይባላሉ?

መ. ከዚህ ሲሄዱ ጎበና ጂዶ ተዋግተው አዲስ አበባ ሲገቡ ተሰማ ጎበና ተብለዋል፡፡

ጥ. ስለዚህ በዚህ ሲገመት ቢያንስ ቢያንስ ከዛ በፊት ትንሽ ጊዜ አለው ማለት ነው?

መ. ብዙ ባላባቶች አሉ ታዋቂ ሰዎችም የዘመቱ አሉ ስለዚህ ነው ከዛ በፊት የተባለው?

ጥ. ያኔ ሲነግሩኝ ካስገበሩ በኋላ ጎበና ቱኬ ማማን ሜሬት ስጠኝ ብለው ጠየቁና ሜሬት ሰጣቸው ብለወኛ ነበር ቁጥሩ ይታወቃል ምን ያህል ለመንግስት ምን ያህል ለባላባት እንደቀረ?

መ. አሁን እኔ የማወቀው ቱኬ ማማ ለመንግስት የሰጠው ሜሬት ምን ያህል እንደሆነ ነው ግን በዛ ወቅት ሜሬቱ በጋሻ የታወቀ አይደለም

ጥ. ጣሊያን አሩሲ ነገሌ መጥቶ ነበር እርሻ ጣሊያን የጀመረ ይመስሎታል?

መ. ጣሊያን እርሻ አልጀመረም

ጥ. ምንም ነገር?

መ. ምንም እርሻ አልጀመረም በጦርነት ላይ ነበር ነገሌ ከማለፍ በስተቀር ብዙም አላረፈበትም ሻሸሜ ነው

ጥ. ቤተርስት ብለው አፄ ኃ/ስላሴ ሲመክርቱ ከሜሬት ተነስተው ነው እንጂ ምንም ነገር አልነበረም?

መ. አዎ ምንም አልነበረም

ጥ. ቤተርስት ስንዴ ለማምረት ነው የተጠቀሙበት ማለት ነው ?

መ. አዎ ቤተርስት ስንዴ ለማምረት ብቻ ነው የተጠቀሙበት

ጥ. ቤተርስት ጣሊያን እንደወጣ አይደለም የተመሠረተው ቆይቶ ነው ማለት ነው?

መ. ቤተርስት የተመሠረተው አፄ ሀ/ስላሴ በ1923 ስልጣን ላይ ወጡ ሚሌት እየከለሉ እያሉ ጦርነት ተነሳ ሚሊሰው ሲያሸንፉ በ1937 ጋሻው ተለካ በድጋሚ በ1942 እንደገና በተሻሻለ ሁኔታ በሚሻም በ1952 ነው

ጥ. እስኪ ስለወረገኑ ይንገሩኝ መቼ ቀረ?

መ. በትክክል ወረገኑ የሚባል ነገር የለም